# Healthy smiles Ontario

### አንተሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች ምንድን ነው (Healthy Smiles Ontario)?

አንታሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች 17 ዓመት እና በታች ለሆኑ ህፃናትና ወጣቶች ነጻ የጥርስ ሕክምና መርሀግብር ነው።

ከ ጃንዮሪ 1, 2016 ጀምሮ በኦንታሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች መርሀግብሮች የተካተቱ፡-

- አንታሪዮ ሥራዎች ስር የጥርስ ሕክምና ጥቅማጥቅሞች፤
- በኦንተሪዮ የአካል ጉዳተኛ ድጋፍ መርሀግብር ስር የህፃናት የጥርስ ሕክምና ጥቅማጥቅሞች፤
- ከባድ የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ሕጻናት እገዛ መርሀግበር ስር የህፃናት የጥርስ ሕክምና ጥቅማጥቅሞች፤
- ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት መርሀግበር (The Children In Need Of Treatment Program)፤
- ኦንታሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች፤ እና
- በአካባቢው የህዝብ ጤና ክፍሎች የሚሰጡ የአፍ ጤና መከላከያ አገልግሎቶች።

### መስፈርቱን የሚያሟላ ማን ነው?

17 እና በታች ለሆኑ ህፃናትና ወጣቶች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

- ኦንታሪዮ ነዋሪዎች ፤ እና
- የገቢ ብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟላ ቤተሰብ አባሎች ከሆኑ።

**ማስታወሻ:** 17 ዓመት እና በታች ለሆኑ ሕፃናት እነርሱ ወይም ቤተሰቦቻቸው፤ የኦንተሪዮ ስራዎች፣ ጊዜያዊ የእንክብካቤ እገዛ፣ ከባድ የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ሕፃናት እገዛ ወይም የኦንተሪዩ አካል ገዳተኛ ድጋፍ መርሀግብር እንዳገኙ ወዲያውኑ ብቁ ሆነው በኦንተሪዩ ጤናማ ፈገግታዎች ይመዘገባሉ። ሌላ የጥርስ ሕክምና መድን ሽፋን ያላቸው ሕፃናትና ወጣቶች ከአሁን በኋላ ወዲያውኑ አይወገዱም።

### እኔ እንዴት እመዘገባለሁ?

- ወደ ontario.ca/healthysmiles ድህረገጽ ይሂዱ
- የኦንተሪዮ የመረጃመስመር አገልግሎት[ServiceOntario INFOline] በነጻ በ 1-844-296-6306 (TTY በነጻ በ 1-800-387-5559) ይደውሉ
- የእርስዎ የአካባቢ የህዝብ ጤና ክፍል ደግሞ እንዲመዘገቡ ሊረዳዎ ይችላል። በእርሰዎ አካባቢ የትኛው የህዝብ ጤና አገልግሎት ክፍል እንደሚሰጥ ለማወቅ ወደ ontario.ca/healthysmiles ድህረገጽ ይሂዱ

አንዴ ምዝገባው እንደተረጋገጠ የኦንተሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች ካርድ ይሰጣሉ። በመርሀግብሩ የጥርስ ሕክምና እንክብካቤ ለማግኘት የጥርስ ህክምና ካርዱ ለጥርስ ህክምና አቅራቢው በእያንዳንዱ ጉብኝት ማቅረብ ይኖርበዎታል።

### ልጄ የጥርስ ሕክምና እንክብካቤ ድንገተኛ የጥርስ ህከምና እንክብካቤን ጨምሮ የት ማግኘት ይችላል?

የጥርስ ሀኪም ካለዎት በኦንተሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች ይሳተፉ እንደሆን ለማወቅ ከእነርሱ ቢሮ ጋር ይገናኙ። የጥርስ ሀኪም ከሌለዎት ለእርዳታ የአካባቢዎን የህዝብ ጤና ክፍል ያግኙ። በእርሰዎ አካባቢ የትኛው የህዝብ ጤና አገልግሎት ክፍል እንደሚሰጥ ለማወቅ ወደ ontario.ca/healthysmiles ድህረገጽ ይሂዱ።

### ምን አገልግሎቶችን ይሸፈናል?

የኦንተሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች ፈቃድ ያላቸው የጥርስ ሕክምና ሰጭዎች፣ እንደ ጥርስ ሀኪም ወይም የጥርስ ንጽህና ጠባቂ ሀኪም መደበኛ ጉብኝቶችን ይሸፍናል። የጥርስ ህክምና አገልግሎቶች የሚያካትተው ክትትል፣ ማጽዳት፣ መሙላት፣ ኤክስሬይ/ጨረር እና ማስተካከልን ይሸፍናል። የኦንተሪዮ ጤናማ ፈገግታዎች አስቸኳይ ወይም ድንገተኛ የአፍ ጤንነት ጉዳዩችን ጨመሮ ይሸፍናል።

### ለምን የአፍ ጤንነት አስፈላጊ ሆነ?

የተቦረበሩ ጥርሶች እና የድድ በሽታ አሰቃይ ሊሆኑ ይችላሉ እንዲሁም ወደ ከባድ ቁስለት/መመርቀዝ ሊያመሩ ይችላሉ፣ የአዋቂ ጥርስ እድገት ላይም ተጽኖ ያሳድራሉ። ስቃይ የእንቅልፍ ማጣትን ሊያስከትል ይችላል፣ የልጁን የመብላት አቅም ይነካል እንዲሁም የልጁን የመማር ችሎታና ት/ቤት መከታተል ላይ እንድምታ ይፈጥራል። ጥሩ የአፍ ጤንነት ለልጀዎ በራስ መተማመን፣ የደህነነት ስሜት እና ለእነርሱ አጠቃላይ ጤንነት አስፈላጊ ነው። የአፍ ጤንነት ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ይከላከሉ!

### ለበለጠ መረጃ፡-

- ontario.ca/healthysmiles ይጎብኙ
- ወይም የኦንተሪዮ የመረጃ መስመር አገልግሎት [ServiceOntario INFOline] ላይ ይደውሉ ፡-

**በነጻ: 1-844-296-6306**
**TTY በነጻ: 1-800-387-5559**
**TTY ቶሮንቶ ብቻ: 416-327-4282**

Catalogue No. 020397 ISBN No. 978-1-4606-7201-3 (PDF) January 2016 © Queen's Printer for Ontario 2016

Ontario